# ለድርድር የማይቀርበው የሕግ የበላይነት

ዋኘው መዝገቡ 03-08-18

ለአንድ ሀገር ሕልውናና ሰላም ለልማትዋም ሆነ ለእድገትዋ ለተረጋጋ ሀገራዊ ሕይወት ቀጣይነት በየትኛውም ግዜ ቢሆን የሕግ የበላይነት መከበር ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሕግ የበላይነት መከበር የአንድን መንግስት በሕግና በስርአት መመራትና መስራት አስረግጠው የሚያሳዩ ተግባራት ናቸው፡፡ የሕግ የበላይነት ከተጣሰ በደምቡና በስርአቱ መሰረት መከበር ካልቻለ በሀገርና በሕዝብ ላይ መጠነ ሰፊ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ የስርአተ አልበኞች መፈንጪያ መሆን ይከተላል፡፡ የሰው ሕይወትና ንብረት ሰላማዊ ሕይወት ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል፡፡

ሕግና ስርአት በአግባቡ ካልተከበረ አንድ መንግስት እንደ መንግሰት ስራውን በአግባቡ ይሰራል ለማለት አያስደፈርም፡፡ የሕግና የስርአት አለመከበር ሀገርንና ሕዝብን ለከፋ አደጋ ይዳርጋል፡፡ የዜጎች ሕይወትም ሆነ ንብረት ምንም አይነት ሕጋዊ ዋስትና የለውም፡፡ በከፋ ሁኔታ ለአደጋ ይጋለጣል፡፡ የአንድ መንግስት ትልቁ ተግባር ሕግና ስርአትን ማስከበር ነው፡፡ ሕግ አውጪውም ሆነ ሕግ አስፈጻሚው ሕገ መንግስቱን አክብረው ለማስከበር የሚንቀሳቀሱት ሕግና ስርአትን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ነው፡፡

ሕግና ስርአት አልተከበርም ማለት በአጭር አገላለጽ መንግስት የለም ወይንም እንደ መንግስት ለመስራት ተስኖታል ማለት ነው፡፡ የዜጎች እለት በእለት የሚኖሩት ሰላማዊ ሕይወት ከታወከ፤ መደበኛ ኑሮአቸውን በሰላም ለመከወን ከተሳናቸው፤ የዜጎች ከቦታ ቦታ በነጻነት የመንቀሳቀስ የመስራት የመኖር ሀብት የማፍራት የመሸጥ የመለወጥ መብታቸው ከተጣሰ፤በሰላም ከቤታቸው ወጥተው መመለስ ካልቻሉ፤ የንግድ እንቅስቀሴው ከተገታ ወዘተ ሕግና ስርአት አልተከበረም ወይንም ተጥሶአል ማለት ነው፡፡

ሕግና ስርአትን ማስከበር በመንግስት ላይ የተጣለ ኃላፊነት ቢሆንም በዋነኛነት ጉዳዩ የሕዝቡ ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም በሚፈጠረው ትርምስ የበለጠ ተጠቂ ተጋላጭ ተጎጂ የሚሆኑት ሕዝብና ልጆቹ ናቸው፡፡ በሕግመንግስቱ መሰረት የሀገርን የሕዝብን ሰላምና ደሕንነት የመጠበቅ ኃላፊነት የመንግስት ነው፡፡ መንግስት ይህን ስራ የሚሰራው ለብቻው ቆሞ ሳይሆን ከሕዝቡ ጋር በመሆን ነው፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የታዩት ከእኛነታችን በእጅጉ የራቁና የተፋቱ ሁኔታዎች አብሮነታችንን የሚሸርሽሩ የሚንዱ ከመሆናቸውም በላይ በታሪካችን ውስጥ ጥቁር ጠበሳ የጣሉ ናቸው፡፡ በጎሳና በብሔረሰብ መነሻነት ግጭት ውስጥ መግባት፤ ንብረት ማውደም፤ አካባቢ ለቀህ ውጣ መጤ ነህ ማለት፤ሕይወት እስከ ማጥፋት መድረስ በእጅጉ አሳዛኝ ክስተት ሲሆን እንዳይደገም ጠንክሮ መስራት ችግሩን ከስሩ መፍታትን ይጠይቃል፡፡ በዚህ መልኩ የሕግ የበላይነት የተጣሰበት ሁኔታም ነው የተፈጠረው፡፡

የሕግ የበላይነት መከበር በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሕግና ስርአት በአግባቡ ካልተከበረ የሰላማዊ ዜጎች መብትና ነጻነት የግል ሕይወትና ኑሮአቸው ሁሉ ዋስትና የለውም፡፡ ሕግና ስርአት እንዲደፈርስ መንቀሳቀስ ሕዝብን ለከፋ አደጋ ከማጋለጥ ባለፈ ፋይዳ የለውም፡፡ ቀድሞ በኖረው የዘመናት ታሪካችን ውስጥ ያልነበሩ አብሮነትን ተከባብሮ፣ ተደማምጦና ተቻችሎ መኖርን የሚንዱ፣ ሕግና ስርአትን የሚያፈርሱ ሀገሪቱንም የከፋ ምስቅልቅል ውስጥ ለመክተት ታቅደው የተፈጸሙ ተግባራት መከሰታቸው እንደ ሀገር ቆም ብለን ለማሰብ ያስገድደናል፡፡

የሕግና የስርአት መፍረስና አለመከበር የመጨረሻ ግቡ የሀገር መፍረስ መሆኑን ከሌሎች ሀገራት ልምድና ተሞክሮ አይተናል፡፡ ሀገሪቱ ከድሕነት ለመውጣት በብድርም ሆነ በራስ አቅም የሰራቻቸው ለሕዝብ የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶች የግለሰቦች ንብረቶች የተለያየ ደረጃ ያላቸው ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች ለሕዝብ አገልግሎት የሚውሉ ድርጅቶች የልማት ተቋማት ጭምር እንዲወድሙ ተደርጎአል፡፡ ይህ የሕግ የበላይነትን መጣስና የመድፈር ድርጊት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሕዝብን ጥያቄዎች በመመለስ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ለሕዝብን ጥያቄዎች ምላሽ የሚገኘው በተረጋጋ ሰላም ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ከሀገር መጥፋትና መውደም ለውጥ እድገትና መሻሻል ይመጣል ብሎ የሚያስብ ካለ ጅልነት ነው የሚሆነው፡፡ የሀገር ንብረት መውደም መጥፋት በየትኛውም መስፈርት የሕዘብ ጥያቄ መሆን አይችልም፡፡ የተገነባውን ሀገር በማፍረስ ሀገር መገንባት ማሳደግ አይሞከርም፡፡ የሚገኝ ትሩፋትም የለውም፡፡ ሕግና ስርአት በፈረሰባቸው ሀገራት የሆነውን የተደረገውን አይተናል፡፡

የየሀገራቱ የጥፋት መነሻ ታሪክ የሚቆራኘው መነሻውም የእኛን የመሰሉ በስሜታዊነት በጭፍን ጥላቻ የታወሩ ለውድመትና ለጥፋት ያሰፈሰፉ አክራሪ ተቃዋሚዎች ሞልተው መትረፋቸው ነበር፡፡ ራሳቸውን ሀገራችውንና ሕዝቡንም ዳግም ማንሰራራት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ይዘውት ጠፉ፡፡

አሁን ባለው ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች አስቀድመው የተከሰቱና የታዩት ሁኔታዎች ሀገራዊና ሕዝባዊ ሰላምን የሚያደፈርሱ የሚያናጉ ከመሆናቸው በላይ የሕግ የበላይነትን የሚጻረሩ ከመሆንም አልፈው ከፍተኛ የሀገራዊ ሀብት ውድመቶችን የዜጎችን ሕይወት መጥፋት ያሰከተሉ ናቸው፡፡

ሀገሪቱ በብዙ ድካምና ልፋት በራስ አቅምም ሆነ በውጭ ብደርና  እርዳታ የሰራቻቸውን ለዛሬው ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድ የሚበጁትን የመንግስትን ፕሮጀክቶችና የሕዝብን ንብረት ማውደም ለሀገሬ የተሻለ አስባለሁ የተፈጠሩት ችግሮች ተስተካክለው ታርመው የሀገሪቱ ልማትና እድገት እንዲቀጥል እሻለሁ ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም፡፡

ወጣቱን በጥላቻ መንፈስ በመሙላት መርዘኛ የሆነ ቅስቀሳ ነዝቶ በማሰለፍ በስሜታዊነት እንዲጋልብ ሆን ተብሎ የሚደረገው የጥፋት ድርጊት ከውስጥ ችግሮቻችን ሌላም በግልጽ የውጭ ኃይሎች እጅ እንዳለበት መጠራጠር አይገባም፡፡ ሕዝብ ለመንግስት ያቀረባቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት ደረጃ በደረጃ ነው፡፡ በተጨባጭ ገዢው ፓርቲ አዲስ የለውጥ ሂደት ለመጀመሩ ማረጋጋጫው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ታስረው የሚገኙ እስረኞች በምሕረት ተፈተው ከቤተሰባቸውና ከሕብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀል መቻላቸው ነው፡፡ ይህ በጎና ትልቅ እርምጃ በእርግጥም ኢሕአዴግ ራሱን በአዲስ የለውጥ ምእራፍ ውስጥ እየመራ እንደሚገኝ ማረጋገጫ አድርጎ መውሰድ ይገባል፡፡ በብዙ መልኩም ለውጦች እንደሚመጡ ይጠበቃል፡፡ለዚህ በመስራትም ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ በሕዝብ ዘንድ የሚጠበቁት ለውጦች ሊመጡ የሚችሉት በሁከት በብጥብጥ በረብሻ፤ መንገድ በመዝጋት፤ ንብረት በማቃጠል፤ስራ በማቆም ከቶውንም ሊሆን አይችልም፡፡ሕግና ስርአት የሕግ የበላይነት መከበር ለሀገራችንም ሆነ ለዜጎችዋ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ በመሆኑ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም፡፡ የተለያዩ ምክንያቶች በመፍጠር የስራ ማቆም አድማ መጥራት፤ ከጸጥታ አስከባሪ ኃይሎች ጋር መጋጨት፤ መንገድ መዝጋት፤ የንግድ እንቅስቃሴውን ማሰናከል፤ ማሕህበራዊ ሕይወትን ማወክ ወዘተ በከፋ መልኩ የሚጎዳው ሕዝቡንና ልጆቹን ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማስተካካል የነበረውን ሰላም ወደነበረበት ለመመለስ የሕግ የበላይነት መከበር ግድ ይላል፡፡ ሕዝብና መንግስት ተቀናጅተው ተናበው መስራትም ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሚፈጠረው ግርግር እንጠቀማለን ብለው የሚያስቡ ሁሉ ይህ አሳቤቸው በእጅጉ የተሳሳተ መሆኑን በሀገርና በህዝብ ላይ ጉዳት ከማድረስ ውጭ አላማቸውን ለማሳካት

እንደማይችሉ ሊያውቁት ይገባል፡፡ የዚህ አይነቱ ግርግር መነሻ ሁኖ ነው በርካታ ሀገራትና ሕዝቦቻቸው የጠፉት፡፡ የወደሙት፡፡

የራሴ የሚሉት መንግስት እስከማጣት የደረሱት፡፡ ለመበታትን የበቁት፡፡ በሚሊዮኖች የተሰደዱት፡፡ የትም መሄድ ያልቻሉት ደግሞ ዛሬም በየቀኑ በአየርና በመድፍ ድብደባ ስር የወደቁት፡፡ ሕጻናት እጅግ ሰቅጣጭ በሆነ ሁኔታ እየረገፉ የሚገኙት፡፡ የሚበላ የሚጠጣ ጠፍቶ የሰው ልጅ በእንዲህ አይነት በምድር ላይ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ልብን በሚሰብር ሰው ሁኖ መፈጠርን በሚያስረግም መልኩ ስቃይ ፈተናና መከራ ውስጥ የወደቁት፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ ማስተዋልና አርቆ መመልከት የተሳናቸው በጥላቻና በስሜታዊነት ተሞልተው ሲደነፉ የነበሩ ሀገርንና ሕዝብን በቅጡ በአክብሮት መመልከት የተሳናቸው የፈለገው መአት ይውረድ ሲሉ የነበሩ አክራሪና ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች ናቸው፡፡

ለመንግስት ለውጥ ሕዝቡን ሲያነሳሱ የተጠቀሙበት ዲሞክራሲ እናሰፍናለን ሰብአዊ መብት እናስከብራለን ነጻ ገበያ እናውጃለን ወዘተ መፈክሮቻቸው በተገቢው ሰላማዊ መንገድ ባለመመራታቸው በሰላማዊ የምርጫ ውድድር ላይ ከመፎካከር ይልቅ በሁከት በአመጽ በነውጥ መንገድ በመጓዛቸው የመጨረሻው ውጤት እንኳን ዲሞክራሲ ሊያሰፍኑ ሰብአዊ መብት ማክበር ደረጃ ሊደርሱ ጭርሱንም ሕግና ስርአት ፈርሶ ስርአተ አልበኝት ነግሶ ሀገራቸውን አውድመው ሕዝብ አልቆ ሁሉም የነበራቸውን አጥተውት ሁሉ ነገር እንዳልነበረ ሆነ ሀገራቸው ወደመች፡፡ሀገሬ የሚሉት እስከማጣት ደረሱ፡፡

የእነሱ ድንቁርና፣ ግትርነትና እልህ ሀገርንና ሕዝብን ይዞ እየጠፋ ነው፡፡ ዛሬ ላይ መጠንቀቅ ያለብንም እንዲህ አይነቱ መመለሻ የሌለው ታሪካዊ ስህተት እንዳይፈጠር ነው፡፡ ከምንም ነገር በላይ የሀገርና የሕዝብ ሕልውና ተከብሮ መኖር የውስጥ ችግሮችን እንደ ሕዝብ በጋራ ተነጋግሮ፣ ተወያይቶና ተደማምጦ መፍታት የሕዝብና የሀገርን ሰላም ማስቀደም ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሕግ የበላይነት  መከበር በእጅጉ አስፈላጊና ወሳኝም ነው፡፡